# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 08 ነሐሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## መውጫው መንገድ - የዜግነት ፖለቲካ !



# ኢዜማ እና የማንነት ፖለቲካ

እኛ ኢትዮጵያዊያን የበርካታ ማንነቶች ባለቤቶች ነን። ከትውልድ ሀረጋችን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋችን፣ ተወልደን ባደግንበት ባህል፣ ከእምነታችን፣ ከፆታችን፣ ከሙያችን እና ከምንገኝበት እድሜ ክልል የወሰድናቸው እና ለእኛ ጥልቅ ትርጉም ያላቸው በርካታ ማንነቶች አሉን። ለትውልድ ሀረጋችን እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ላለው ባህልና ወግ የተሰጠው እውቅና መጠን፤ ለአፍ መፍቻ ቋንቋችን መዳበር እና ለእምነት ተቋሞቻችን መከበር፤ ለፆታ እኩልነት፤ የወጣቱ ትውልድ እድሎች እና የመሳሰሉ ከማንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ያሳስቡናል። በመሠረቱ ለራሳችን የምንሰጠው ክብር ከምንለካባቸው መንገዶች አንዱ ለማንነታችን መገለጫዎች በምንሰጠው ክብር ነው።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ኢትዮጵያዊያን ላሏቸው በርካታ ማንነቶች ተገቢውን አክብሮት የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን የአንዱ ማንነት ከሌላው ጋር ሳይጋጭ ተደጋግፈውና ተከባብረው በእኩልነት የሚያድጉበት ሥርዓት ለመገንባት የተዘጋጀ ፓርቲ ነው። ለዚህ ምስክሩም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ናቸው።

1. ኢዜማ በመንደር፣ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ያሉ አባላት (grassroots) የሚመሩት ንቅናቄ የፈጠሩት ድርጅት ነው። በዚህ ደረጃ ሕዝብ ውስጥ ለመግባት ጥረት የሚያደርግ ድርጅት ለትውልድ ሀረግ፣ ለቋንቋ፣ ለባህል፣ ለእምነት፣ ለፆታ፣ ለዕድሜ እና የመሳሰሉ ማንነቶች ከፍተኛ ቀረቤታ እና ተቆርቋሪነት እንዲኖረው፤ ሆኖም በእነዚህ ማንነቶች መካከል ቅራኔ ሳይሆን ትብብር እና መደጋገፍን እንዲያጎለብት ተፈጥሮዉ ያስገድደዋል።
2. ኢዜማ ዘርን መሠረት አድርጎ የተነሳ ድርጅት አይደለም፤ ሆኖም በኢትዮጵያ የሚገኙ ነገዶች፣ ብሔረሰቦችና ብሔሮች ተከብረው እንዲኖሩ፤ ቋንቋዎቻቸውና ባህሎቻቸው እንዲዳብሩ ይታገላል። የቡድን መብቶች የሰብዓዊ መብቶች አካል መሆናቸው ኢዜማ ይረዳል። በብሔር፣ ብሔር ሰብ፣ ነገድ ወይም ዘውግ ሳቢያ አድልዎ እንዳይፈፀም መታገል የኢዜማ ቀዳሚ ዓላማ ነው። የቡድን መብቶችን ለማስከበር ግን በብሔር፣ ብሔረሰብ መደራጀት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ብሎ ያምናል።
3. ኢዜማ የሀይማኖት ፓርቲ አይደለም፤ ሆኖም በኢትዮጵያ የሚገኙ ሁሉ ሀይማኖትና የእምነት ተቋማት ተከባብረው እንዲኖሩ ይታገላል። የእምነት ነፃነት የሰብዓዊ መብት አንድ አካል እንደሆነ ኢዜማ ይረዳል። በሀይማኖት ምክንያት አልድዎ እና መገለል እንዳይፈፀም መታገል የኢዜማ ዓላም ነው። የእምነት ነፃነትን ለማስከበር ፓለቲካን በእምነት መደራጀት ከጥቅሙ ጉዳት ያመዝናል ብሎ ያምናል።
4. ኢዜማ የወንዶች ወይም የሴቶች ብቻ ፓርቲ አይደለም። ይልቁንም ወንዶችም ሴቶችም እኩል መሆናቸውን በመረዳት የሁለቱም ፆታዎች አባላት እኩል ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የሚጥር ድርጅት ነው።
5. ኢዜማ የአዛውንቶች ወይም የወጣቶች ብቻ ፓርቲ አይደለም። ይልቁንም ዕድሜው ለፓለቲካ ተሳትፎ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚሳተፍበት የሁሉም የዕድሜ አባላት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚጥር፤ ከዚህም አልፎ በአካል ጉዳት፣ በጤና ጉድለት፣ በትምህርት ደረጃ ወይም ሌላ ማናቸው ምክንያት አድልዎ እንዳይፈፀም የሚታገል ድርጅት ነው።
6. ሁሉም ማንነቶቻችን እንዲታወቁ እና እንዲከበሩ የምንፈልገው «ኢትዮጵያ» በምትባለው ውዷ ሀገራችን ውስጥ በመሆኑ ማንነቶቻችንን ለማስከበር እና አድልዎና መድልዎችን ለማጥፋት የምናደርገው ትግልም መሠረቱ ኢትዮጵያ መሆን አለባት ብሎ ኢዜማ ያምናል።

በኢትዮጵያዊነት መደራጀት የብሔር፣ ብሔረሰብ ማንነቶችን መጨፍለቅ ወይም የእነሱን ጉዳይ ወደ ጎን መግፋት ማለት በፍጹም አይደለም። ይልቁንም በኢትዮጵያዊነት መደራጀት ሁሉን ብሔር፣ ብሔረሰቦች በእኩልነት መመልከት፤ እና በመካከላቸውም አውዳሚ ቅራኔ ሳይሆን ጤናማ መደጋገፍ እንዲኖር መሻት ማለት ነው። በኢትዮጵያዊነት መደራጀት ማለት የእምነት ጉዳዮችን ቸል ማለት አይደለም። ይልቁንም በኢትዮጵያዊነት መደራጀት ማለት የሁሉን እምነቶች እኩልነት ተቀብሎ ለሁሉም እምነቶች ተቻችሎ መኖር መታገል ማለት ነው። ለማኅበራዊ ፍትህ መታገል ማለት ማንነትን መሠረት ያደረጉ መድሎዎች እንዳይፈፀሙ መታገል ማለት ነው። ይህ ትግል ፍሬያማ እንዲሆን ግን ሁሉንም ማንነቶች በእኩልነት በሚያይ አቃፊ ኢትዮዮጵያዊ ማንነት ላይ መመሥረት ይበጃል። ይህ ነው የኢዜማ የማንነት ፓለቲካ ፍልስፍና።

ኢዜማ ኢትዮጵያን ለሚቀጥሉት ምዕተ ዓመታት የሚያሻግር ፓርቲ ለማድረግ እንጣር።



## “ኢዜማ ሙስናን የሚጠየፍ ባህል ያለው ፓርቲ እንዲሆን የፋይናንስ ሕግና ደንቡን በጥብቅ ተግባራዊ እናደርጋለን።”

የጁአልጋው ጀመረ የበጀትና ፋይናን ኃላፊ/ትሬዠረር

ነሐሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




ለአዲስ አበባ ለሚገኙ የምርጫ ወረዳ ከፍተኛ አመራሮች የፓርቲውን የፋይናንስ መዋቅር፣ የፋይናንስ ፖሊሲ፣ የፋይናንስ ሰነድ ዝግጅትና አመዘጋገብን እንዲሁም ፋይናንስ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጠ፡፡

በሥልጠናው መክፈቻ ላይ የተገኙት የኢዜማ ም/ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) “ሥልጠናው የተማከለ የጋራ አስተሳሰብ ይዞን ለመሥራት ያስችለናል፡፡ ከዚህ ውስጥ የተሻለ እውቀት ያለው፣ በቂ ትንተና መስጠት የሚችል አይጠፋም፡፡ ጊዜውና አቅሙ ያላችሁ ወረዳችሁ ላይ፤ እንዲሁም ወደ ሌሎች ቦታዎች ሄዳችሁ ማሠልጠን ይጠበቅባችኋል፡፡” ብለዋል፡፡

የበጀትና ፋይናንስ ኃላፊ የሆኑት የጁአልጋው ጀመረ በበኩላቸው “ኢዜማ ሙስናን የሚጠየፍ ባህል ያለው ፓርቲ እንዲሆን፤ የፋይናንስ ሕግና ደንቡን በጥብቅ ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ ሁላችሁም ኃላፊነት በተሰጣችሁ የምርጫ ወረዳ በተመሳሳይ መሥራት ይገባቿኻል፡፡” በማለት ንንግራቸውን የጀመሩ ሲሆን “መንግሥት በአሁኑ ወቅት International Finance Reporting System (IFRS)ን እየተጠቀመ ነው፡፡ ፓርቲዎችንም በIFRS ተጠቀሙ የሚል ከሆነ ከማዕከል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ሥልጠና በመስጠት በቀላሉ መጠቀም እንጀምራለን” ብለዋል፡፡

ከሥልጠናው በኋላ የፋይናንስ ኃላፊው፡- “ሥልጠናው በተሳካ ሁኔታ መጠናቁን፤ ከፋይናንስ ኃላፊዎች በተጨማሪ የየወረዳዎቹ ሊቀመንበሮችም ሥልጠናውን አብረው መውሰዳቸውን በመጥቀስ በተሰጣቸው ሥልጠና መሠረት ሊሠሩም ይገባል፣ እኛም አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርጋለን፡፡” ብለዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ በሚገኙ ለ23ቱም የምርጫ ወረዳ ላይ ላሉ ለኦዲት ኮሚቴ አባላት ሥልጠና መሰጠቱ ይታወሳል፡፡










## አድራሻ


ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ነሐሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መውጫው መንገድ - የዜግነት ፖለቲካ !

## 1.እንደመግቢያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአንድ በኩል የረጅም ዘመን ገናና ታሪክ፣ ሰፊ የተፈጥሮ ፀጋ ባለቤትና እንደጉንጉን አበባ የፈኩ ባህሎች መድረክ በመሆን ስትታወቅ፤ በሌላ ወገን፣ በመቋጫ አልባ ድርቅና ጠኔ፣ እጅግ አስከፊ በሆኑ የእርስ በእርስ ጦርነቶች፣ የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የሚታፈኑባት ሀገር በመሆንና አጠቃላይ ኋላቀርነቶች ተምሳሌት ተደርጋ ስለመወሰዷ በሕይወት ዘመናችን የውርደት ማቅ የደረብነው፣ የአገዛዝንም ገፈት የቀመስነው የዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን እማኞች ነን፡፡ ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ደግሞ በሕዝብ ፈቃድ የተቋቋመ መንግሥት ወይንም የተረጋጋ፣ ደርዝ ያለውና የዘመነ የፖለቲካ ሥርዓት ባለቤቶች አለመሆናቸውን የችግሮቻችን ሁሉ እናት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## 2.ፖለቲካን በጨረፍታ

ፖለቲካ የሚለው ቃል በከተሜ ኢትዮጵያውያን መዝገበ ቃላትና የዕለት ተዕለት ተዋስኦ ተዘውትሮ የሚነሳ ቢሆንም፣ ለገጠሬው ኢትዮጵያዊም ቢሆን እንግዳ ቃል ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይሁን እንጂ ቃሉ ያዘለው ፅንሰ-ሀሳብ አያሌውን የሀገራችን ዜጋ ይቅርና ልሂቃንን እንኳን በውል በሚያግባባ ተተንትኗል ወይንም ያግባባል ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ግርድፍ የሆነው ለፖለቲካ የምንሰጠው የወል ትርጉምም ቢሆን ሲበዛ አሉታዊ እንደምታና ትርጉም ጥላውን ያጠላበት ስለመሆኑ አያከራክርም፡፡

ምንም እንኳን ቀደም ብለን እንዳየነው ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የመንግሥትነት ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም አሁን በውል የምንረዳው ዘመናዊ ፖለቲካና የፖለቲካ ትግል ግን ከግማሽ ምዕተ-ዓመት ያልዘለለ ታሪክ እንዳለው መስማማት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ዘመኑ ቢያጥርም የተፈጠሩት የፖለቲካ መነቃቃቶችና እነርሱን ተከትለው የተከሰቱት የፓለቲካ ፍንዳታዎችና ተያያዥ መቋጫ አልባ ቀውሶች የሀገራችን የታሪክ፣ የአንድነትና የቀጣይ ህልውና መሠረቶች በኃይል ያናወጡ ስለመሆናቸው አሌ አይባልም፡፡

የፍንዳታዎቹ ተከታታይ ግርሻ ደግሞ አሁን ሀገራችን ለምታልፍበት የድህነት አዘቅትና አይን ለሚወጋ የጭቆና ሌሊት አስተዋፆው ከፍ ያለ ነው፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በፖለቲካ በተለወሱ ግጭቶች ዳፋ አሳሩን ሲበላ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፖለቲካን የዕኩይ ግብሮችና ሀሳቦች ሁሉ መገለጫ አድርጎ የማየት ዝንባሌውም ከፍ ያለ ነው፡፡ አንዳንዴ ፖለቲካን አፍታቶ ለማሳየት ሲሞከርም በማር የተለወሰ እሬት አድርጎ የመቀበል እንጂ የማኅበረሰብን ሕይወት የሚለውጥ ወሳኝ መሳሪያ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

### ለመሆኑ ፖለቲካ ምንድን ነው?

እንደብዙ ሰርዎ-ቃሎች ሁሉ ፖለቲካ የሚለው ቃል ስርዎ-መሠረትም ከግሪክ የተወሰደ ሲሆን በተለያዩ ቋንቋዎች ተባዝቶ እና ተወራራሽ ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን፡፡ ፍጥረቱ (Polis) ከሚል ስርዎ-ቃል ሲሆን የትርጉም ይዘቱም ከመንግሥትና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር የተዛመደ ነው፡፡ በተለምዶ በስዩመ እግዚአብሔርነት ወይንም በአፈ-ሙዝ አስገዳጅነት ያለ ሕዝብ ፈቃድ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ የተጫኑ ኃይሎችንም ከምር መንግሥታት ወይንም መንግሥት የሚል ስያሜ ብንሰጣቸውም ትክክለኛና ተገቢ ሆኖ አናገኘውም፡፡ ምክንያቱም ዜጎች ከሉዓላዊ ሥልጣናቸው ቆርሰው ለጥቅሞቻቸው፣ ለክብራቸውና ለመብቶቻቸው መከበር የተገደበ ኃላፊነት በተገደበ ጊዜ እንዲከውን ፈቅደውና ወደው ውል የሚያስሩለት ብሎም የሚፈጥሩት አካል ነውና መንግሥት፡፡ ሕዝብ ከመንግሥት ጋር ለሚያስረው ውል መሠረት የሚሆነው ደግሞ በሕዝበ ውሳኔ የፀደቀ ርዕሰ-ህግ (ህገ-መንግስት) ነው፡፡ ያለሕዝብ ይሁንታ የሚጫኑበት ኃይሎች አገዛዞች እንጂ መንግሥታት አይደሉም፡፡ ሕዝብ ከመንግሥት ጋር በሚያስረው ውል መንግሥት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ የሚከበሩለት ጥቅሞችና መብቶች እንዳሉት ሁሉ ዜጎች (ሕዝብ) ይህንን በመሠለው ፖለቲካዊ መስተጋብር ወደና ፈቅዶ የሚገባቸው የውዴታ ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡ ይህንን ስምምነት የሚያስከብር ሕግ ወይንም የፍትህ ሥርዓት ደግሞ ሁነኛ የውሉ ህልውና መሠረት ይሆናል፡፡ ህግም ሆነ መንግሥት ዜጎች ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም ጥቅሞቻቸውን የሚያስከብሩባቸውና ጊዜያዊና ቀጣይ ዙሪያ መለስ ደህንነቱን የሚያረጋግጡባቸው መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ ከፍ ባለ ቁጥር ከእነዚህ ተቋማት ዜጎች የሚያገኙትም ጥቅምም ከፍ ይላል፡፡

ፖለቲካ በዜጎች ሁሉ እጣፋንታ ላይ በአዎንታዊ ወይም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ተፅዕኖ የሚያሳድር፣ ብንሸሸው የሚከተለን፣ ብንተወውም ፈጽሞ የማይተወን ከሁለንተናችን ጋር በውል የተቆራና ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል አርስቶትል “Man is a political animal” ወይም “ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው” ያለው፡፡ ነገር ግን ፓለቲካ ከብሔር ጋር የተቆራኙበት ሕዝብና ሀገር ሰኔና ሰኞው የገጠመበት ነው፡፡

## 3.ዜግነት ምንድን ነው?

የራሱ የሆነና በውል የሚታወቅ፣ ድንበር፣ ባንዲራ፣ ታሪክ፣ ባህል (ባህሎች)ና ሌሎች መገለጫዎች ያሉት በሕግና ሥርዓት በሚተዳደር ሉዓላዊ ሀገር ጥላ ስር የሚኖሩ ሰዎች በሕግ በተደነገገው መሠረት የሚኖራቸው የሀገር ባለቤትነት፣ በሀገራቸው እጣ ፋንታ ላይ በእኩልነት የመወሰን፣ ያለአድልኦ የመስተናገድ ወይንም አገልግሎት የማግኘት መብት፣ የዜግነትን ክብርና ግዴታ በሕግ አግባብ እንደተደነገገው የተጎናፀፉት መብት ዜግነት ወይንም የዜግነት መብት ይባላል፡፡ የዜግነት ቃል-ኪዳን ዜጎች በተናጠል የሚገቡት እንጂ በቡድን የሚጎናፀፉት አይደለም፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ በህግ በተደነገገው መሠረት የሀገሩ፣ የንብረቱ፣ የሕይወቱና የሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ባለቤት ነው፡፡ ሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች በዚያ ሀገር ጥላ ስር በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩ ነገር ግን የዜግነት መብትን ወይንም ክብርንና እውቅናን አይጎናፀፉም፤ በህግ የተደነገገውን መስፈርት እስኪያሟሉ ድረስ፡፡



## 4.ፖለቲካና ዜግነት

ዜግነትና ፖለቲካ ምን ያክል የተሳሰሩ ጽንሰሃሳቦች እንደሆነ ለመገንዘብ “ግለሰብ” (Individual) በሚለው ሃሳብና “ዜጋ” በሚለው ሃሳብ መካከል ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ለይቶ ማየት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ በፊዉዳል ወይም በየትኛዉም አምባገነን በሆነ ሥርዓት ውስጥ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች አሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ግን ሰብዓዊ መብታቸዉ የማይከበር ወይም ዴሞክራሲያዊ፣ ሲቪልና ፖለቲካዊ መብት የተነፈጉ ግለሰቦች ስለሆኑ ዜጎች ብለን ልንጠራቸዉ አንችልም፡፡ ምክንያቱም ዜግነት ማለት “መብት የማግኘት መብት” ማለት ነዉና! አንድ ግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብቱና ነጻነቱ የተከበረ እንዲሆን ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። ግለሰቦች መብትና ነጻነት እንዲኖራቸዉ ሰብዓዊ ፍጡር ከመሆናቸዉ ባሻገር የአንድ የዜጎቹን መብትና ነጻነት የሚያከብር እና የአባልነት ብቸኛ መመዘኛዉ ዜግነት የሆነበት የፖለቲካ ማኅበረሰብ አባል መሆን አለባቸዉ። የዜግነት ፖለቲካ የሚለውና ዛሬ አገራችን ዉስጥ በስፋት በመደመጥ ላይ ያለዉ ጽንሰ ሃሳብ የሚመነጨዉ ከእንደዚህ አይነቱ ፖለቲካዊ ፍልስፍና አስተሳሰብ ነዉ።
ፖለቲካን በጨረፍታ ለመዳሰስ ስንሞክር ፖለቲካ ከመንግሥት ጋር የተቆራኘ መሆኑን አውስተናል፡፡ መንግሥት ደግሞ በእውነትም መንግሥት የሚሆነው በኃይል ሲጫን ሳይሆን ዜጎች ከማይገሰስ ሉዓላዊ ሥልጣናቸው ቆርሰው ጉዳያቸውን ያስፈጽምላቸው ዘንድ በህግና በጊዜ ገድበው ሥልጣን የሰጡት እንደሆነ ነው፡፡ አብርሃም ሊንከን ተዘውትረው እንደሚታወሱበት “ከሕዝብ፣ ለሕዝብና በሕዝብ” የተቋቋመ መንግሥት ነው እውነተኛ ሉዓላዊ መንግሥት፡፡ ከዚህ ውጭ ስዩመ-እግዚአብሔር ቢሆንም ስዩመ-ጠመንጃ ሁለቱም አገዛዞች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ዜጎች ለረጅም ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል እስካሁን ድረስ የሚያደርጉት ከአገዛዞች ወደ ስዩመ ሕዝብ ወይንም ወደ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለመሸጋገር ነው፡፡

ፖለቲካና ዜግነት አንዱ ከሌላው ውጭ ህልው የሚሆኑበትን ደረቅ መሬትን ማግኘት አሳር ነው፡፡ ከመንግሥትና ከዜጎች ቁርኝት ውጭ ፖለቲካ እንዴት ይታለማል? ዜግነትስ በሀገር ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉን አቀፍ መብቶችን ካላጎናፀፈ ምኑን ዜግነት ሆነ? ዜጎች የማይዘውሩት ፖለቲካስ እንዴት የተሟላ ትርጉም ሊኖረው ይችላል? ፖለቲካ ተጀምሮ እስኪያልቅ ከዜግነት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡
ፖለቲካና ዜግነት የተቆራኙትን ያህል የዜግነት መብትም በጅምላ የሚቸር ወይንም የሚነፈግ አይደለም፡፡ ዜግነት ከመብትና ግዴታ ወይንም ተጠያቂነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ አንድ ዜጋ የአንድ ብሔር አባል በመሆኑ በግል ከሚኖርበት ተጠያቂነት አያመልጥም፤ መብቱንም አይገፈፍም፡፡ የአንድ ብሔረሰብ አባል በመሆኑ የጅምላ ፍረጃ ወይንም የደቦ ፍርድ ሰለባ ሊሆን አይገባውም፡፡

አንድ ዜጋ በፖለቲካ መስተጋብሩ እርከን ከዝቅተኛው እስከመጨረሻው የመሰላሉ እርከን ሊወጣ የሚችለው፣ አሊያም በፍትህ ሚዛን ጎድሎ (አጉድሎ) ሲገኝ የከፋ ቅጣት ሰለባ የሚሆነው ከዜጋው እኩይ ወይንም በጎ ምግባር ጋር በተገናኘ እንጂ የዚህ ወይንም የዚያኛው ብሔር፣ ጎሳ ወይንም ዘር አባል በመሆኑ ወይንም ባለመሆኑ አይደለም፡፡ ምንአልባትም አጠቃላይ ፖለቲካን የምናይበት የተንሸዋረረ አታያይና የተሳሳተ ስሌት አሁን ለምንገኝበት ቅጥ አንባሩ ለጠፋበት የፖለቲካ ውድቀትና ዙሪያ መለስ ድቀት አስተዋፆው ከፍ ያለ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የሳለፍናቸው 28 የአገዛዝ ዓመታት ወትሮም ውል አልባ የነበረውን የሀገራችንን የፖለቲካ አወቃቀር የከፋ ውጥንቅጥ ውስጥ ከቶታል፡፡ የሀገር ባለቤትነት በሕገ መንግሥቱ የተሰጠው ለዜጎች ሳይሆን “ለብሔር ብሔረሰቦች፣ ህዝቦችና” የሚል አንዱ ከሌላው እንኳን በምን እንደሚለያዩ የማይታወቅ ስያሜ ውስጥ ወድቋል፡፡ የዜግነት ክብር በኢትዮጵያ ስለመሙላቱ በሀገሪቱ ብሔራዊ መዝሙር ቢዘመርም በተግባር ግን ዜግነት እውቅና የተነፈገበትን እውነታ መጋፈጥ ግዴታ ሆኖአል፡፡ ፖለቲካችን ከፍ ያለ ግራ መጋባት ውስጥ ወድቋል፤ ምክንያቱም በዜግነት ላይ ያልተመሠረተ ፖለቲካ ህልው ያልሆነ ፖለቲካ ተምሳሌት ነው፡፡ ፖለቲካው ከዜግነት ተነጥሎ ለብሔረሰቦች ሲሞሸር የጌታና የሎሌን ሥርዓት ለማንበር ሁነኛ መደላድል ሆኖአል፡፡ የጎንዮሽ ግንኙነቱም ላይ ትልቅ የመፈራቀቅና የመጠፋፋት ስጋትን ጋርጧል፡፡

ዜጋው በአስተሳሰቡ ልህቀት፣ በሥነ-ምግባሩ፣ በግብሩ ጥራትና ለሀገሩ በሰነቀው ርዕይ ላይ ተመስርቶ ከየትኛውም የኑሮ እርከን፣ ከየትኛው ብሔረሰብ፣ ከየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ወይንም ከየትኛውም ሀይማኖት መገኘቱ ተቀናሽም ተደማሪም ነገር ሳያስከትል፣ ግለሰቡ በግሉ ኃላፊነት የሚወስድበት፣ የሚመርጥ የሚመረጥበት የሉዓላዊ ሥልጣኑን ባለቤት ሊሆን ይገባዋል፡፡

## 5.ዜግነት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

ዜግነት ዜጎች በሀገራቸው እጣ ፋንታ፣ ሀገራቸው የምታቋድሳቸው ተረፈ-ፀጋ፣ መብቶች እና ግዴታዎች ያለአድልኦ የሚሳተፉበት በሕግ እውቅናና ጥበቃ ያለው እድል መጎናፀፍ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ ባልሰፈነባቸው ሀገሮች ነገሩ ለየቅል ነው፡፡ የፍትህን ሀሁ የማያውቁና የዴሞክራሲም ሽታ የሌለባቸው ሀገሮች ዜጎች እንዳሏቸው ይናገራሉ፤ ዜጎችም እንዲሁ ነን ይላሉ፡፡

በሀገራችን ቀደም ባለው የነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ በዜጎችና በባሮች መካከል የነበረው ግንኙነት የጌታና የሎሌ እንጂ በሉዓላዊ ዜጎች መካከል የነበረ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ጥቂት ባለአባቶች በብዙሃኑ ንብረትና ሕይወት የሚያዙበት ሁኔታ ነበር፡፡ ፍትህ ለዜጎች እኩልነትና ልዕልና ያልቆመበት ገንዘብና ባላባታዊና መሠረት ያለው የሚያሸንፍበት ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የዜጎች ክብር፣ ጥቅምና ልዕልና የገዥዎች አንጡራ ሀብት ቢሆንም ይኸንን የሚያስተካክል ፍትሃዊ ሥርዓት አልነበረም፡፡

ውሎ አድሮም የዜጎች መበደል የተማሪዎችን የሠራተኞችንና የገበሬዎችን አመፅ ቀስቅሶ የአገዛዙን ግብዓተ-መሬት አፋጠነው፡፡ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም የሚለው መፈክር የብዙሃንን ቀልብ የገዛ ቢሆንም ወታደራዊ መንግሥት ተቋቋመ፤ የዜግነት ክብርን፣ ፍትህና ዴሞክራሲም ውሃ በላቸው፡፡ ዜጎች ሉዓላዊ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው መሪዎቻቸውን መምረጥና ለመሪነትም መመረጥ ይቅርና የሕይወታቸውንና የንብረታቸውን ዋስትና የሚያረጋግጥ የፍትህ አካል አልነበረም፡፡ ሁሉም በአንድ አብዮታዊ መሪ፣ ሁሉም በአንድ የእዝ ሰንሰለት ስር ገባ፡፡ ሥርዓቱ ግን ዴሞክራሲያዊ የሚለው ተቀፅላ አልቀረበትም፡፡ ይኸን የመሠለው ሥርዓት በመውደቁ የሚፀፀት ይኖር ይሆን?

ምን አልባት የደርግ ውድቀት የዜግነት ልዕልና የነገሠባት ዴሞክራሲያዊነት ኢትዮጵያን ያዋልድ ይሆናል የሚል ተስፋ እንደነበር መካድ አይቻልም፡፡ አዲሱ የብሔር ፖለቲካን ተገን አድርጎ የተተከለው አገዛዝ ከወትሮዎቹ ይልቅ ስለዴሞክራሲ በመስበኩ እንኳን በጭቆና

ቀንበር ስር የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ መታለሉ አልቀረም፡፡

ይሁን እንጂ የአገዛዙ ግብርና ቃል ፈጽሞ ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡ ለዴሞክራሲ እውነተኛ መሠረት የሆነው ዜጋው ተዘንግቶ መብትና ሀገር ለብሔረሰቦች ተሰጡ፡፡ ዜጎች መንደራቸውን እንጂ ሀገራቸውን እንዳያልሙ ቀን ከሌት ተሠራ፡፡ የይስሙላ የዴሞክራሲ ተቋማት በዜጎች ላይ መሪር ቀልዳቸውን ያለ ለከት ቀጠሉ፡፡ የፍትህ ቤተ-መቅደስ የሚሰኙት ፍርድ ቤቶች ፍትህ የምትሰቀልበት አደባባይ ሆኑ፡፡

ዜጎች በትክክል ዜጎች ሊሰኙ የሚችሉት በባላባታዊ ሥርዓት፣ በወታደራዊ መንግሥት አሊያም የዘውግ ፌደራሊዝም አይደለም፡፡ ዜጎች በእውነትና በእኩልነት መብታቸው የሚከበረው የዜጋውን መብት የተቀበለ፣ በዚህም መሠረት ላይ እውነተኛ የፍትህና የዴሞክራሲ ተቋማትን በገነባ የፖለቲካ ሥርዓት ነው፡፡ የፍትህና የዴሞክራሲ ተቋማት ባበቡበት ሀገር የዜጎች ልዕልናም ያብባል አስተማማኝ ዋስትናም ያገኛል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሣት ያለበት አንድ ቁም ነገር እናንሳ፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ሲባል ግለሰቦች

## 6.መውጫው መንገድ - የዜግነት ፖለቲካ

ሀገሮች በህላዌያቸው የተለያዩ ዘመኖች የተለያዩ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ የሀገሮች አንድነትና የዘመኑ መሪዎችም ፅናት ይፈተናል፡፡ ብዙ ታላላቅ ሀገሮች ወደ ታላቅነት ማማ የወጡት ለችግሮች ተሸንፈው ከመበታተን ይልቅ ለአያሌ ቀጣይ አመታት ሐገራቸውን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለማስቀጠል የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት በመቻላቸው ነው፡፡ በችግሮች ከመረበሽ ይልቅ ችግሮችን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የሀገሮቻቸውን ዱካ ፈትሸው የሚመጣውን መንገድ መጥረግ በመቻላቸው ነው፡፡

ከብሔረሰቦች ጥያቄ ጋር የተያያዘው የእኛ ሀገር ችግር ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሠራሽ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል፡፡ የዘመናችን ኢትዮጵያ አንኳር ችግሮች ተብለው ከሚቆጠሩት መካከል አንዱ ነው፡፡ ችግሩን አቅልለን ባየነው ቁጥር የሀገራችንን ህልውና እስከመፈታተን የሚገዝፍ ችግር መሆኑን እያስተዋልን ነው፡፡ ስለዚህ ዘመኑንና ችግሩን በሚመጥን ብስለት ችግሩን ለመፍታት ከችግሮቹ ተምረን ነገን ብሩህ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ልንፈታቸው ይገባል፡፡ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ችግር ውስጥ ያስገቡን መንገዶች በመከተል ከችግር ለመውጣት መሞከር ግን ከሁሉ የከፋ ውድቀትን ያስከትላል፡፡

አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን ማንም ስለአሀዳዊ መንግስት ምሥረታ የሚሰብክ አይደለም የሚጠቅስ የፖለቲካ ኃይል ባይኖርም አንዳንዶች የዜግነት ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ ወገኖች አሀዳዊ ሥርዓትን ሊጭኑብን ነው ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ እውነቱ ግን ፈጽሞ ይኸ አይደለም፡፡ አሀዳዊ አስተዳደርን ለመጫን የሚመኙም ካሉ ሀሳባቸውን ለሕዝብ አቅርበው በሕዝብ ድምጽ ሊሸነፉ ወይንም ሊያሸንፉ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ዋናው ቁምነገር ግን "ሲወለድ ያጠለቀውን ሲሞት አወለቀው" እንዲሉ በልጅነታቸው ከተዋሃዳቸው የፖለቲካ ትርክት መላቀቅ ስለተሳናቸው እንጂ አሀዳዊ ሥርዓትን እያቀነቀነ የሚገኝ ፓርቲ ኖሮ አይደለም፡፡ በቀናነት የተሰነዘረና ካለማወቅ የሚመነጭ ስህተት ከሆነ ግን እውነቱ ኢዜማ የዜግነት ፖለቲካን ቢያራምድም የአሀዳዊ መንግሥት አድናቂም የሀሳቡም አቀንቃኝ

> «የምንጋራቸው ማንነቶች ከሚለያዩን ማንነቶች ይልቅ ይሰፋሉ፤ ይበዛሉም፡፡ ስለዚህ የሚለያዩን ማንነቶች በማክበር የጋራ ማንነቶቻችንን መሰረቶች በማጠናከርና የመፃኢ ዘመን ህልሞቻችንን በመትለም እነርሱንም እውን ለማድረግ በብርቱ ልንሠራ ይገባናል፡፡»

በዘፈቀደ የሚኖኙበት ማለት አይደለም፡፡ በሕግና ሥርዓትና በጥብቅ የተጠያቂነት መንፈስ የሚመሩበት እንጂ፡፡ እንዲሁም የዜግነት ፖለቲካ ስንል ዜጋው በራሱ ደሴት ይኖራል ማለታችን አይደለም፡፡ ማኅበራዊ ቁርኝቶች ይበጣጠሳሉ ማለታችን ፈጽሞ አይደለም፡፡ ዜጋው ተፈጥሮአዊ መብቱን ተጠቅሞ የመሠለው ህጋዊ ቡድን ውስጥ አባል የመሆን መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ መሠረታዊው ቁም ነገር፣ የዜጋውን ሉዓላዊነት ተቀብሎ ዜጋውን ለማክበር ያልቆረጠ ኃይል የብሔሮችን መብት ሊያከብር አይችልም፡፡ ማንም የነፃ አውጭነት ካባ ቢደርብ፣ ስለብሔሮች መበደል የአዞ እንባውንም ቢረጭ የዜጋውን መብት የማያከብር የቡድኖች መብት አያከብርም፡፡ በጥቂቱ የማይታመን በብዙ ሊታመን አይችልምና፡፡

መሞከር እንጂ ችግሩ በተፈጠረበት መንገድ ለመፍታት መሞከር የውድቀት መንገድ ነው፡፡ ችግሩን ያመጣውን ቫይረስ በመውጋት በሽታን ለመከላከል የሚቻለው ለክትባት ብቻ ነው፡፡ ከዘር ጋር ተያይዞ የመጣን ችግር የዘውግ ብሔርተኝነትን በማስፋፋት መፈወስ ሳይሆን ማክፋት ነው መጨረሻው፡፡

የጽሑፉን ይዘት ላለማስፋት በማሰብ ዘልቀን አልገባንበትም እንጂ የምንጋራቸው ማንነቶች ከሚለያዩን ማንነቶች ይልቅ ይሰፋሉ፤ ይበዛሉም፡፡ ስለዚህ የሚለያዩን ማንነቶች በማክበር የጋራ ማንነቶቻችንን መሰረቶች በማጠናከርና የመፃኢ ዘመን ህልሞቻችንን በመትለም እነርሱንም እውን ለማድረግ በብርቱ ልንሠራ ይገባናል፡፡ እንዲሁም በእኛ ዘመንም ይሁን ባልነበርንባቸው ዘመኖች የተፈጠሩ ችግሮችን ከየትኛውም አቅጣጫ በማንም ቢፈፀሙ በእውነትና ከስሜት በፀዳ መልኩና ፈጽሞ አይደለም፡፡

ነገር ግን የፌደራል ሥርዓቱ ባህልን፣ ቋንቋን፣ የልማት አመችነትንና ሌሎች ወሳኝ መስፈርቶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊዋቀር ይገባል የሚል የፀና አቋም አለው፡፡ የፌደራል ሥርዓቱን ልዩነቶችን በሚያሰፋ መልኩ በማዋቀር ችግሮችን ከመቀፍቀፍ ይልቅ ችግሮችን በሚፈታና ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ማዋቀር ተገቢ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ዜጎች በየአካባቢዎቻቸው ያሉ ችግሮቻቸውን የማይሸራረፍ ሉዓላዊ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው የመፍታት ሙሉ ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አላቸውም፡፡

ነገም ከዚህም የከፋ ሀገራዊ ችግር ሊገጥመን ይችላል፡፡ ቢገጥመንም ሊገርመን አይገባም፡፡ ነገር ግን ችግሮችን በሚያወሳስብ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ለመፍታት ከመሞከር



ይልቅ ችግሮች ተፈጥሮአዊ በመሆናቸው ሁልጊዜም ሊገጥሙን ይችላሉና የችግር አፈታት ስልቶችን፣ ባህሎችንና አቅማችንን ማዳበር ለነገ የሚባል አይደለም፡፡ ዜጎች የእኔ ነው ብለው የሚታመኑበት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሊቋቋም የሚችለው ሀገርም ተረጋግቶ ለምቶና ዘምኖ ሊቀጥል የሚችለው ፖለቲካና ዜግነትን መሰረት ያደረገ መስተጋብርን ተከትለን መንግሥታችንን ስናዋቅር ነው፡፡ ይህን በማድረግ ፋንታ ቋንቋም አልነው ብሔር አሊያም ዘርን መ ሠ ረ ት አ ድ ር ገ ን በበቀለኝነትና በተረኝነት መንገድ ሀገርን እናስቀጥላለን የሚሉ ጤነኛ ፖለቲካኞች ሊኖሩን አይችሉም፡፡

አሁን እንደምናስተውለው አንድን ክልል እንኳን ነጻ እናወጣለን የሚሉ የተለያዩ ድርጅቶችን እናያለን፡፡ እርስ በእርሳቸው የሚፎካከሩት ደግሞ ማን የተሻለ አክራሪ መሆኑን ለማስረገጥ በመማሰን ነው፡፡ እንዲሁም የሌሎች ክልሎች ነፃ አውጭዎች ነን ከሚሉ ኃይሎች "የፈጠርኩትን ቴክኖሎጂ ሰረቃችሁኝ" በሚል መሰል ተቃርኖ ተወጥረው ሕዝብን ደም ሊያቃባ በሚችል ጎዳና ላይ እየተመሙ ነው፡፡ የአንዱ ብሔር ነፃ አውጭ የሌላው ክልል ነፃ አውጭ በህልውናው ላይ እንደዘመተበት ይቆጥራል፡፡ ቁም ነገሩ ማንም ያድርገው ማንም እንዴትም ቢያሸሞነሙኑት አንድን ብሔረሰብ ብቻ ማዕከል አድርጎ የሚቀየስ የትግል ስልት የአጥፍቶ ጠፊነት መንገድ ስለመሆኑ በሰዎች ሞትና በሚሊዮኖች መፈናቀል የምናስረግጠው እጅግ ኋላቀርና ዘመኑን የማይዋጅ የትግል ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት ቀደም ከግራ ፖለቲካ የተቀዳ ሲሆን አሁንም ምንም እንኳን የብሔር ፓርቲዎች በይፋ ግራ ዘመም ወይንም ሶሻሊስቶች ነን ብለው ባያውጁም በተግባር እየፈፀሙ ያሉት ያው ጥንት በተማሪዎች እንቅስቃሴ ጊዜ ከእነስታሊን የተቀዳ ሀሳብ ስለመሆኑ በጥቂቱ ተጠግቶ ግብራቸውን ማየት ብቻ በቂ ነው፡፡ መነሻውም የጠላትና ወዳጅ ትርክት ነው፡፡

ለግማሽ ምዕተ-ዓመት የተጓዝንበት ቋንቋን መሠረት ያደረገ አደረጃጀት ምን እንዳስገኘልን፣ ምንም እንዳከሰረን ለመናገር ከዚህ በላይ ተጨማሪ ሚሊዮኖች መፈናቀል የለባቸውም፣ ንፁሃንም ባመኗቸው ወገኖቻቸው መታረድ የለባቸውም፡፡ የዘውግ ብሔርተኞች ዛሬ "የእኛ" የሚሉት ብሔር አባራሪ "የእነርሱ" የሚሉት ደግሞ ተባራሪ አድርገው እያሰቡ ይሆናል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ካሰቡ ተሳስተዋል፡፡ በትግራይ ሕዝብ ስም እስካሁን ሲምል ሲገዘት የነበረው ሕወሃት ለትግራይ ሕዝብ እዳ እንጂ ትሩፋት አልሆነውም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ለዓመታት በፍቅርና በክብር ከወገኖቹ ጋር ተሳስሮ ከሚኖርባቸው አካባቢዎች በኃይል እንዲወጣ ሲደረግ በስሙ የማለው ሕወሃት አንዳች አልፈየደለትም፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ፣ በሚሊዮን ተዋልዶና ተዋህዶ ከኖረበት ክልል በገፍ ሲፈናቀል አንድም በኦሮሞ ሕዝብ ስም የተደራጀ ድርጅት ኦዲፒን ጨምሮ ሊታደገው አልቻለም፡፡ የጌዲዮ ሕዝብ ቅስምን በሚሰብር ሁኔታ በገፍ ሲፈናቀል የደቡብ ሕዝቦች ድርጅትም ሆነ ሌላ በጌዲዮ ስም የተደራጀ ድርጅት መድህን አልሆነውም፡፡ ገና በኢሕአዴግ የሥልጣን ማለዳ ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ የሰቆቃን ገፈት እየተጎነጨ ያለው የአማራን ሕዝብ የትኛውም በዘር የተቧደነ ድርጅት ሲታደገው አልተሰተዋለም፡፡ እንዲያውም በየክልሉ ያሉ በተለይ በዘር ከመደራጀትም ባሻገር የተለያዩ አካባቢዎችን እየመሩ ያሉ የብሔር ፓርቲዎች ከሕዝብ ጀርባ መሽገው ግጭቶችን እያፋፋሙ እንዳሉና ዋነኛ መንስኤዎች ስለመሆናቸውም ለመረዳት ነቢይ መሆንን አይጠይቅም፡፡ ከዚህ የምንረዳው በብሔር የተደራጀ ኃይል ሀገርን መቀመቅ ከማውረድ ባለፈ የትኛውንም ብሔር ፈፅሞ መታደግ አለመቻሉን ነው፡፡ አሜሪካኖቹ እንደሚሉት የተሻለ ህብረትና የተሻለ ውህደት እንፍጠር ወይንስ ከዚህ ወደከፋ የመለያየት አዘቅት እንውረድ? የትኛው መንገድ ይሻለናል? በሰነድ ላይ የሰፈሩ ቃላት በራሳቸው ሰይፍ አይደሉም፡፡ ሕገወጡን ከሕጋዊው አይለዩም፡፡ ኢ-ሞራላዊውን አስወግደው ሞራላዊውን አይተኩም፡፡ ሀሳቦችን በባለቤትነት የሚሸከሙ ብሎም ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት ወሳኝ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ባልተሟላበት ሁኔታ ቃላት ከወረቀት ላይ ነብርነት ዘለው አያውቁም፡፡

> «ገና በኢሕአዴግ የሥልጣን ማለዳ ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ የሰቆቃን ገፈት እየተጎነጨ ያለው የአማራን ሕዝብ የትኛውም በዘር የተቧደነ ድርጅት ሲታደገው አልተሰተዋለም፡፡»

በመሆኑም ተቋማትን በማጠናከር፣ ፍትህ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ በእነርሱም መሠረት ላይ የሚሰፍንም ሰላምና ታላቅ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መፍጠር ይገባል፡፡ የአንዱ ባህል ለሁሉም ጌጡ፣ የአንዱ መጨቆን ለሁሉም ውርደቱ ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል፡፡ የወገኑ አይደለም የማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር መጎሳቆል፣ መበደል፣ መፈናቀልና መሰደድ ስሜት የማይሰጠው ዜጋ ካለ እርሱ በጥልቅ የ ስ ነ - ል ቦ ና ስብራት ውስጥ ስለመሆኑ ነጋሪ አያሻውም፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ለ ኢ ት ዮ ጵ ያ ይገባል ሲባል ከአሳማኝ ትንታኔ በመነሣት ብቻ አይደለም፡፡ በየትኛውም የሀገራችን ክፍልም ሆነ በዓለም ዙሪያ ተበትኖ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ለገዛ ወገኑና ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ የሚሳሳ የሚጨነቅና አክብሮቱን የሚቸር ጨዋና ለጋስ ሕዝብ መሆኑን የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን በልቡም በነፍሱም አትሞ የሚዞር ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዜግነት ፖለቲካ ለም መሬት ነው፡፡ ሕይወቱ፣ ባህሉና ዓላማው ኢትዮጵያዊነት ነውና፡፡

ያም ሆኖ አሁን የተንሰራፋው ዘርን መሠረት ያደረገ ሀሳብ በወጣቶቻችን ልብ ላይ በተወሰነ ደረጃ ፍሬ ማፍራቱን አንዘነጋም፡፡ በዚሁ ዘርን መሰረት ያደረገ አደረጃጀት ምክንያት ታሪካችን ጠልሽቷል፡፡ የሕዝባችን የአንድነት የደህንነት መሠረቶች ተናግተዋል፤ተስፋውም ያለማቋረጥ ጥያቄ ውስጥ እየገባ ነው፡፡ ችግሩን አቅልሎ ማየት አይቻልም፡፡ ከችግሩ ጋር ተመቻችቶ መኖር ፍጹም ኢ-ሞራላዊና ኢ-ምክኒያታዊ ነው፡፡ ችግሩን ተጋፍጦ መርታት ግን ከእውነተኛ የመርህ ባለቤቶችና የትግል ሰዎች ይጠበቃል፡፡ የኢዜማም ምርጫ ይኸው ነው፡፡

የዘር ሸንቁርን እያሰፉ የልዩነት ገደል ከመፍጠር በጋራ ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ እየመከሩ መግባባት፤ መግባባትም ካልተቻለ በሰለጠነ አያያዝ ችግሮችን መፍታት ትልቅነት ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ጥቂት ወጣቶችን ገጀራና ነፍጥ በማሸከም ወደ መንደራችን እንዳትዘልቁ የሚል አያያዝ የዘር ፖለቲካን የሰከነ ሀሳብና የተሰለቀ ስሌት ባለቤት አለመሆኑን ከማሳየቱም በላይ በደመነፍስ የሚነዳ ባዶ

የስሜት ፖለቲካ መሆኑን በገሃድ ያሳብቃል፡፡ አንድን አካባቢ እንደ አፀደ እንስሳት በመቁጠር በውስጡ የሚኖሩ ዜጎች የምትሰሙትም ሆነ የምትሰሩት እኛ የምናምንበትን ብቻ ነው የሚሉ ወገኖች በሰው ልጅ የእድገት ደረጃ ላይ እጅግ ዝቅተኛው እርከን ላይ እንደሚገኙ አያሻማም፡፡

ሀሳቡ ስህተት ብቻ ሳይሆን ከስብዕና እርከን ፈፅሞ የሚያወርድ የውድቀት አዘቅት ነው፡፡ ሰው ያልሆነ የብሔረሰብ አባል የለም፡፡ ሰውን መሠረት አድርጎ የማይፈታ ችግርም የለም፡፡ የታመመውንና የታሰረውን ስለመጠየቅ ምስኪኑን ስለመታደግ እንዲቆሙ፣አንዱ ብሔር የእዚህ እምነት ብቻ ተከታይ ነው የማይበልበት ሃይማኖቶችን የሚከተል ዜጋ በሞላበት ሀገር በመንደር አጥሮ መኖር በምን ምክንያት ተገቢ ሊሆን ይችላል?

የገዥ መደብ ደሙን ያላፈሰሰው፣ ለይቶ ዘብ የቆመለት፣ በአይኑ ብቻ ሳይሆን በልቡ እንዲያነባ በመከራ ወላፈን ያልገረፈው፣ በርሃብና በጠኔ ያላንዘፈዘፈው የትኛውን ሕዝብ ነጥለን ማውጣት እንችላለን? የጭቆናው ለምጥና የመከራው ሰንበር ያልጎረበበት የትኛው ብሔረሰብ ይሆን? አብሮ የተጨቆነ፣ የደማ ያነባ፣ የታመመ፣ የታረዘ ሕዝብ አይደለምን? ጭቆናና በደል አሁን ድረስ የምንወደው ሕዝቡ እያለፈበት ያለ ሰርጥ አይደለም? አብሮ ሊቆም ይገባዋል ወይንስ ተነጣጥሎ? የዘር ጉዳይ ፍጹም ያልነበረና ወደፊትም የማይኖር አድርጎ ማቅረብ ተገቢና አሳማኝ አይሆንም፡፡ አሁንም ልናጣጥለው የምንችለው ጉዳይ እንዳልሆነ አይተናል፡፡ በጥንቃቄ ልንይዘው የሚገባ ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ካለፉ በደሎች ተምሮ እነርሱንም በይቅርታና በእርቅ ዘግቶ እንዳይደገሙ መትጋት፣ እስካሁን ያልተጓዝነውን መጓዝ፣ የተበላሸውን አርመን የተሻለችና ለልጆቻችን የተስፋ ምድር የምትሆን ሀገር የምንፈጥርበት እንጂ በዘር ተበጣጥሰን ሀገራችንን አንሰን የምናሳንስበት፣ ልጆቻችንም በሀፍረት አንገታቸውን የሚሰብሩበት ውርስ ልንተውላቸው ፈጽሞ አይገባም፡፡

የተነገሩ ትርክቶች በየሕዝባችን ክፍል ውስጥ ቁጣና ቁጭት አልተፈጠሩም ማለት አይቻልም፡፡ ሁሉም ብሔርን መሠረት አድርጎ የሚነሳ “ነፃ አውጭ” እንደሚታወቀው ከጠላት ነው የሚጀምረው፡፡ ሌላው በገነት ሲኖር እርሱ በሲወል እቶን ሲለበለብ እንደነበር ያልተነገረው ብሔረሰብ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም፡፡ ያለፈውን መሰረዝ ወይንም መለወጥ እንደማይቻል እንተማመን፡፡ ካለፈው ለትምህርታችን የሚሆነውን እንውሰድ፡፡ ዛሬን በትክክል መኖር ነገንም ዛሬ ላይ በአግባቡ ለመሥራት እንትጋ፡፡ ትናንት ላይ ተቸክሎ ዛሬን ማክፋት ነገንም ማጨለም ግን በየትኛውም መመዘኛ ፈፅሞ ማነስ፣ ኢሰብዓዊነትም ነው፡፡ ወደ ኋላ እያዩ ወደፊት ለመራመድ የሚሞክሩ የብሔረሰብ ድርጅቶች ትግላቸው ከትናንት ጋር ነው፡፡ ከትናንትም ወደ ከፋ የኢሰብዓዊነት ጉርጅ እንደሚያወርዱን ዛሬ በሀገራችን የምናየው ከሃምሳ ዓመት የብሔር ጥያቄን ያነገቡ ወገኖች ትርክትና ትግል በኋላ የደረሰንበት ሁኔታ ያሳያል፡፡ የብሔር ፖለቲካ አቀንቃኞች ዘመንና ሁኔታዎች ቢቀየሩም እነርሱ ግን መነፀር አልቀየሩም፣ አይቀይሩም፡፡ ሌኒንና ስታሊም ቢሞቱም ሀሳባቸው ግን ከእኛ የብሔር ፖለቲከኞች ዘንድ አልሞተም፡፡ በሞተ ሃሳብ ሀገርና ትውልድ እየገደሉ ቀጥለዋል፡፡ መቀጠልም ይፈልጋሉ፡፡ ሊፈቀድላቸው ግን አይገባም፡፡ የልጆቻችን ዓለም በዘር መነፅር እንዲንሸዋረር በሂደትም መፃኢ እድላቸው እንዲጨልም አንፈቅድም፡፡

ቁጣ አይኑር ባይባልም ቁጣ ግን ወደ ትክክለኛው መፍትሄ አያመጣንም፡፡ ሕዝቡ በጋራ ሊጎናፀፈው ከሚችለው ታላቅነት ይልቅ በበደለኝነት ስሜት እስኪጠፋፋ ድረስ ተስፋ ቢስነት ቤት እንዲሠራበት አናድርገው፡፡ ቁጣ ወደ ጥላቻ እየተቀየረ ጥለቻ ወደለየለት ዘረኝነትና መጠፋፋት ገደል እየወረወረን ነው፡፡ በቁጣም ሆነ በጥላቻ ላይ ተመስርተን የምናራምደው ፖለቲካ በትክክል ለሕዝብ ሊበጅ አይችልም፡፡ እንዲያውም ከታለመለት ውጤት በተቃራኒው እንጂ፡፡ የመቀራረብ፣ የመተዛዘን የመረዳዳትና አብሮ የመበልፀግን መንገድ አጥቦ፣ የመለያየትንና የመጠፋፋትንና የኢሰብዓዊነት ጎዳና እንደሚያሰፋ ምስክር አያሻውም፡፡ ችግራችን በአንድ ምሽት እንዳልተፈጠረ ሁሉ በአንድ ምሽት አይጠፋም፡፡ በሰከነና በሠለጠነ ለዜጎች ሁሉ ክብር ግድ በሚለው የፖለቲካ ሥርዓት ግን እንደሚስተካከል መተማመን ይቻላል፡፡ የጃጀ ዘመንን፣ የደረቁ አፅሞችንና የቀረ ሀሳብ ላይ ተቸክለን የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር፣ ብሎም ሀገርን ማዘመን አይቻልም፡፡

“የብሔር ፖለቲካን” የሚያቀነቅኑ ወገኖች ገና ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ የሰው ልጅ በብሔር ፌደራሊዝም የተዋቀረ እስኪመስል ድረስ ትክክለኛ ስለመሆኑ ሊነግሩን ይሞክራሉ፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታው የማታውቀውን ዘርን መሠረት ያደረገ የንፁሃን እልቂትና መፈናቀል ያስተናገድነው በዚሁ በዘር ፌደራሊዝም ዳፋ መሆኑን ማንም ሊስተው አይችልም፡፡ በዘር ፖለቲካ ባሳለፍነው አንድ ዓመት ብቻ እንኳን የሆነው የዘር ፖለቲካ የሲኦል መንገድ ስለመሆኑ ሁነኛ ማስረጃ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከሰብዕናው ሊነጠሉ የማይችሉ ሉዓላዊ መብቶችን ተጎናፅፎ የተፈጠረ መሆኑ እየታወቀ የግለሰቡን መብት ደምስሶ በብሔር ማደራጀት ሰው የተባለውን ፍጡር ፈጽሞ ካለማክበርና መብቱን በማን አለብኝነት ከመግሰስ ውጭ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ ዋና ዓላማውም በብሔር ስም ብዙሃን ሳይሆኑ ጥቂቶች ፈላጭ ቆራጭ የሚሆኑበትን መደላድል መፍጠር ነው፡፡ በራሺያም ሆነ በሀገራችን ያየነውም ይኸው በብሔሮች ስም የጥቂቶች ከዚያም ሲያልፍ የአንድ ግለሰብን ፈላጭ ቆራጭነት ማስፈን ነው፡፡ ዴሞክራሲም ሆነ ፍትህ ለብሔር በጅምላ የሚታደሉ አይደሉም፡፡ ብሔርን ከዴሞክራሲ ማያያዝ እውነተኛውን ዴሞክራሲ ለመድፈቅ መዝመት ነው፡፡ ምክንያቱም ጥቂቶች ለብሔሩ እናውቅልሃለን በማለት አዲስ ገዢዎች ሆነው ከመውጣት ባለፈ ከአገዛዝ ወደ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግሩት አይችሉምና፡፡ ፍትህም ቢሆን በጅምላ ለዚህ ወይንም ለዚያኛው ብሔር የሚታደል ሬሽን አይደለም፡፡ ፍትህ በግለሰቡ በጎ ወይንም አሉታዊ ተግባር ላይ ተመሰርቶ የሚሰጥ ግለሰቡም ተጠያቂ ወይንም ነፃ የሚሆንበት ሂደት ነው፡፡ በፍትህ መሠረት ላይ የሚገኝ ሰላም፣ በሰላም መሠረት የቆመች ዴሞክራሲያዊት ሀገር፣ መገንባት የሚቻለው በመሰረቱ የዜጋውን መብት መነሻ በማድረግ ለቡድን መብቶችም እውቅናና ጥበቃ የሚያደርግ ሥርዓት ሲፈጠር ነው፡፡ ለዘመናት ከምንዳክርበት የፖለቲካ ዝፍት ልንወጣ የምንችለው ዜግነት መሠረት ባደረገ ፖለቲካ ነው፡፡





# የፊታችን ቅዳሜና እሁድ በአርሲ ስሬ እና በደሴ ሕዝባዊ ውይይት እንደሚካሄድ ተገለጸ።

ነሐሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የፊታችን ቅዳሜ ነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ስሬ ወረዳ መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲሁም እሁድ ነሐሴ 26 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራ ክልል ደሴ ከተማ ባሕል አምባ አዳራሽ በፓርቲው ፕሮገራምና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከአባላት እና ደጋፊዎች ጋር ሕዝባዊ ውይይት ለማድረግ ቅድመ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ተጠሪ ዋሲሁን ተስፋዬ ገልጹ። እንደ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገለጻ ቅዳሜና እሁድ ይደረጋሉ ተብለው የሚጠበቁ መርሃ ግብሮች ፓርቲው ሊያደርጋቸው በእቅድ ከያዛቸው ሀገር አቀፍ ንቅናቄዎች አካል መሆናቸውንና ለሕዝባዊ ውይይቶቹ መሳካት የአካባቢዎቹ የምርጫ ወረዳ ተጠሪዎች ከፓርቲው ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ እየሠሩ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎቹ የተለየ ችግር ካልገጠመ በቀር በተከታታይ በተያዘላቸው የግዜ ሰሌዳ በመላ ሀገሪቱ እንደሚካሄዱ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገልጸዋል።

# ኢዜማ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ጋር ይወያያል

ነሐሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ከሚገኙ ወጣት አባላት እና ደጋፊዎች ጋር ነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ባህል እና ቲያትር አዳራሽ (ማዘጋጃ ቤት) ውይይት እንደሚያካሂድ ተገለጸ፡፡ በውይይቱ ላይ የመነሻ ጹሁፍ በድርጅት ጉዳይና በወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ እንደሚቀርብም ታውቋል፡፡ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ጋር በወቅታዊ የሀገሪቷ ሁኔታ በተመለከተ፣ ኢዜማ ከተመሠረተ ጀምሮ የተሠሩ ሥራዎችን ምን ምን እንደሆኑ እና ወጣቱ ከኢዜማ ምን ይጠበቃል፣ ኢዜማስ ከወጣቱ ምን ይጠብቃል? በሚሉ ጉዳዮች ለመወያየት አላማ ያደረገ ዝግጅት እንደሆነ የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ ቴዎድሮስ አሰፋ ገልፀዋል፡፡ በውይይቱ ላይ ጥሪ የተደረገላቸው የተለያዩ እንግዶች፣ የኢዜማ አመራሮች እንዲሁም የኢዜማ አባላትና ደጋፊ የሆኑ ከ1200 በላይ ወጣቶች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በዕለቱ ከተሳታፊዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በፓርቲው አመራሮች ምላሽ የሚሰጡ ሲሆን በውይይቱ ላይ ወጣቶች በመገኘት ያለገደብ ጥያቄ በማንሳት፤ ሃሳብ በመስጠት እንዲሳተፉ ለአዲስ አበባ ወጣቶች ጥሪ ቀርቧል፡፡ በውይይቱ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ወጣቶች በየሚኖሩበት አካባቢ ከሚገኙ የኢዜማ የምርጫ ወረዳ አደራጆች ጋር በመገናኘት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚችሉም ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የጸደቀው ሕግ እና ሴቶች



አዲሱ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ከረቂቁ ላይ በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገውለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነሐሴ 18 ቀን 2011 ዓ.ም. በአስቸኳይ ስብሰባ ፀድቋል። አዋጁ የፆታ እኩልነት የሚያበረታቱ አንቀፆችን ይዟል። ለአብነት ያህል አንቀፅ 13(6) የምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ሲያቋቋም ገለልተኛ በስነምግባራቸው የታወቁ ወንድ እና ሴት አባላት እንዲኖሩት ይደነግጋል። በተጨማሪም ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍን በተመለከተ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸውን የሴት እጩ ተወዳዳሪዎች፣ የሴት አመራሮችና አባላት ብዛት እንደመስፈርት ያስቀምጣል።

ነገር ግን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በረቂቁ የተካተተውን "እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል:: ሆኖም እኩል ድምጽ ካገኙት ተወዳዳሪዎች ወንድና ሴት ከሆኑ ድጋሚ ምርጫ ማካሄድ ሳያስፈልግ ሴቷ እጩ እንድታልፍ ይደረጋል::" የሚለውን አንቀፅ 61(3) ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 35 የሴቶች መብት ድንጋጌ ጋር ይጣረሳል በማለት ውድቅ አድርጎታል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ካሏት ዜጎች ውስጥ 51 በመቶ ያህሉ ሴቶች ናቸው። ሆኖም ሴቶች የቁጥራቸውን ያህል በተለያዩ የኢኮኖሚ ማኅበራዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ውስጥ ተሳትፏቸው ውስን እና እጅጉን አናሳ ነው። ለምሳሌ ምንም እንኳን በፆታ ንፅፅር እኩል ካቢኔ ቢኖርም በፓርላማ ውስጥ ካሉት 547 መቀመጫዎች 38.8 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው በሴቶች የተያዙት።

የሴቶች ተሳትፎ ለምን ያስፈልጋል? ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና የሀገር እድገት የኅብረተሰቡን ማንኛውም አካል ወደ ጎን በመተው ሊሳካ እና ሙሉ ሊሆን አይችልም። ከዚህም በተጨማሪ ተሳትፎ የዴሞክራሲና የውክልና ጉዳይ ነው። ሴቶች እንደሴት ለመብታቸው በሚሞግት እና በሚሠራ አካል የመወከል መብት አላቸው። ላለፉት በርካታ ዘመናት ሴቶች ውሳኔዎች በወንዶች ሲወሰኑላቸው ኖረዋል። ወንዶች የሴቶች ጉዳይ አይመለከታቸውም ማለት ሳይሆን 'እስከመቼ' ድረስ የሚለው ዋናው ጥያቄ ሲሆን ለነሱ አንገብጋቢ ጉዳይ ለሌሎች ላይሆን ይችላል ነው።

ሴቶችን እንዴት ወደመድረኩ ማምጣት፣ እኩል ተሳታፊ እና የመብቶቻቸው ተጠቃሚ ማድረግ እንችላለን? የሴቶችን አቅም መገንባት እና ማበርታት እንዲሁም ኅብረተሰብን ማስተማር ብዙውን ግዜ የሚነሳው ሃሳብ ነው። ከዚም በተጨማሪ መንግሥታት በፖሊሲ እና በሕጎች በማስደገፍ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ይጥራሉ። ከነዚህም መካከል ሴቶች በበታችነንት እና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን እና እየደረሰባቸው ያለውን ችግር ከግምት በማስገባት፣ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እና ለማረም በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች (affirmative action) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። የምርጫ ረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 61(3)ም የዚህ የድጋፍ እርምጃ አካል ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ሴት ህፃናት ከትምህርት ቤት ቀርተው ያለእድሜያቸው ይዳራሉ። በርካታ ሴቶች ይደፈራሉ፣ ጠለፋም ይካሄድባቸዋል። በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሰዎች ሴትን የማስተማር፣ ውሳኔን የሚጠይቁ ኃላፊነቶችን የመስጠት ጥቅምን አልተረዱም። ሴቶችም በቤተሰብ እና በኅብረተሰብ ውስጥ ልጅን የማሳደግ ቤተሰብን የመንከባከብ ከፍተኛ ኃላፊነት ስለሚጣልባቸው አስተዳደራዊ ሥራዎችን መሥራት ፈታኝ ይሆንባቸዋል።

የምርጫ ተወዳዳሪ የሆነች አንዲት እጩ ከአንድ ወንድ ጋር እኩል ድምፅ ስታገኝ ቀጥታ ማለፍ አለባት የሚለው አንቀፅ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው ምንም እንኳን ሁለቱም በርካታ መሰናክሎችን አልፈው ሊመጡ ቢችሉም ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ለኢትዮጵያ ሴቶች የጋራ እውነት ነው። ይህ አንቀፅ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚጣረስ ሳይሆን እንደውም የሴቶች መብት ድንጋጌ ጋር የሚደጋገፍ ስለሆነ አንቀፁ መፅደቅ እና መካተት ነበረት።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከተገለፀው አንቀፅ አንፃር የፆታ እኩልነት ወይም የሴቶች መብትን በተለይም የልዩ ድጋፍ ሁኔታ ሲነሳ፣ በሕገ መንግሥት መደንገጉን እንደማረጋገጫ መውሰዳቸው ሁለት ነገሮችን ካለመረዳት የመጣ ነው። አንደኛ የችግሩን ውስብስብነት አለመረዳት ነው። ሁለተኛ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 35(3) ልዩ ድጋፍ የሴቶች መብት አካል መሆኑን አለመረዳት ነው። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች ውስጥ ይህ ልዩ ድጋፍ በተለያየ መልኩ ተካቷል። ለሴቶች የፆታ እኩልነት ሕገ መንግሥት ላይ ስለሰፈረ ብቻ ሊረጋገጥ አይችልም። እጅግ ትልቅ ጥረትን ይጠይቃል። ከጥረትም በላይ ሌሎች ይህ ችግር መሰናክል ሆኖባቸው የቀሩ ሴቶችን የማየት እና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ቅን ልቦናን ይጠይቃል (ለሁሉም የተገለሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ይሠራል።)

ኢዜማ የሴቶችን እኩልነት እንዲሰፍን በተግባር እየሠራ ይገኛል። ችግሮችን ለመረዳት እንዲሁም ከፓርቲው ጀምሮ ለውጥ ለማምጣት ይጥራል። የልዩ ድጋፍ ሁኔታንም ከምስረታው ጀምሮ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። ለምሳሌ ለጠቅላላ ጉባኤ ከሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የሚላኩ 3 አባላት ሲኖሩ የምርጫ ወረዳዎች ተጨማሪ 1 ሴት እና 1 አካል ጉዳተኛ መወከል ይችላሉ። ይህም ወረዳዎች ሴቶችን እና አካል ጉዳተኞችን ስላሳተፉ ተጨማሪ የመወከያ ድምፅ እንዲያገኙ ስለሚያደርግ ሴቶችን እንዲያሳትፉ ይገፋፋቸዋል።

ኢዜማ ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያገል ፖለቲካ ውጤታማ እንደማይሆን ይገነዘባል። የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት የምትጥር ሀገር በሁሉም ዘርፍ የፆታ እኩልነት በማስፈን ማንኛውም ዜጋ ወደኋላ እንዳይቀር ቁርጠኝነት ሊታሳይ ይገባል ብሎ ያምናል። ይህም በሁሉም ፖሊሲ እና ሕግ መንፀባረቅ ይኖርበታል፣ ይህንንም ለማሳካት በፕሮግራም እና ደንብ አካቶ ፖሊሲዎችም ላይ እየሠራበት ይገኛል።